# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የግብርና ሚኒስቴር

# የአትክልት፣ ፍራፍሬና ስራስር ምርት ግብይት

# መመሪያ ቁጥር ----/2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

---------/ 2015 ዓ.ም

# መመሪያ ቁጥር …… 2015 ዓ.ም

# <u>የአትክልት፣ ፍራፍሬና ስራስር ምርት ግብይት መመሪያ</u>

በአገራችን ኢትዮጵያ የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ግብይትን፤ ኋላቀር ከሆነ ልማዳዊ ሥርዓት በማላቀቅ፤ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓትን በመዘርጋት በህግ እንዲመራ ማድረጉ፤ ለአምራቹ እና በግብይት ሂደቱ ለሚሳተፉ ሁሉ ፍትሀዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ ባሻገር ለጠቅላላው አገራዊ ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚያበረክተው አስተዋጾ የላቀ በመሆኑ፤

ወቅታዊ የገበያ መረጃ ለአምራቹ፣ ሸማቹ እና የንግድ ማህበረሰብ ተደራሽ የሚሆንበት፤ የገበያው ሰንሰለት የሚያጥርበት፣ የግብይት ሂደቱን የሚያውኩ ሕገወጥ ተግባራትን መከላከልና መቆጣጠር የሚቻልበት፤ እንዲሁም ተጠያቂነት የሰፈነበት ሥርዓትን መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በፌደራል መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 በአንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 1/ (ወ) ለግብርና ሚኒስቴር የተሠጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት ይቻል ዘንድ በአንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት ይህ የአትክልት ፣ ፍራፍሬና ስራስር ምርት ግብይት መመሪያ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

   ይህ መመሪያ “የአትክልት፣ ፍራፍሬና ስራስር ምርት ግብይት መመሪያ ቁጥር ------ /2015” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **“አትክልት”** ማለት ቅጠሎቻቸው፣ አበባቸው፣ ፍሬአቸው፣ ግንዳቸው፣ ኮረታቸውና እምቡጣቸው ወይም እሸታቸው ለምግብነት የሚውሉ ምርቶችን ያካትታል፤
2) **“ስራስር”** ማለት ስራቸው ለምግብነት የሚውሉ እንደ ጎደሬ፣ የሀረግ ቦየ፣ ድንች፣ ስኳር ድንች፣ እንሰት የመሳሰሉት የስራስር ምርቶች ናቸው፤
3) **“ፍራፍሬ”** ማለት እንደ ብርቱኳን፣ ሙዝ፣ አቡካዶ፣ አናናስ፣ ማንጎ፣ ፓፓያ መንደሪን፣ ሎሚ፣ ዘይቱን እና የመሳሰሉትን የፍራፍሬ ምርቶች ይጨምራል፤
4) **“አምራች”** ማለት ማንኛውም አትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር በማምረት ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ትነው፤
5) **“ምርት”** ማለት በማንኛውም አትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር በማምረት ሥራ ላይ በተሰማራ ሰው የተመረተ የአትክልት፣ ፍራፍሬና ስራስር ውጤት ነው፤
6) **“ገበያ”** ማለት በአካባቢ፣ በሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ደረጃ የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርቶች የሚቀርቡበት ቦታ ሲሆን የኤሌክተሮኒክስ መገበያያንም ያካትታል፤
7) **"ግብይት"** ማለት የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት እና አገልግሎትን ከአምራቹ እስከ ተጠቃሚው ደርሶ ጥቅም ላይ እስከሚውል በልውውጥ ሂደቱ ያሉ ተግባራትን የሚያካተት ነው፤
8) **“የግብይት ተሳታፊ”** ማለት በአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ግብይት የሚሳተፍ አምራች፣ ጅምላ ነጋዴ፣ ቸርቻሪ፣ ከሰብሳቢ አቅራቢ፣ ላኪ፣ አቀናባሪ፣ በቀጥጣ ተጠቃሚ ሸማችን እና የህብረት ስራ ማህበራትን ያጠቃልላል፤
9) **“ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት”** ማለት የታለሙ የንግድ ልውውጦችን ከደንበኞቻቸው ጋር የሚያገናኝ ሁለንተናዊ፣ ቀልጣፋ፣ በመረጃ ላይ የተመሰረተ፣ በዘመናዊ የግብይት አካሄድ፣ የፈጠራ አስተሳሰብ፣ ምርምርን፣ ስትራቴጂን፣ ቴክኖሎጅን እና ትንተናን የያዘ የግብይት ስርዓት ነው፤
10) **“ሸማች”** ማለት ለማምረት ሥራ ወይም መልሶ ለመሸጥ ሳይሆን ዋጋውን ራሱ ወይም ለራሱ ወይም የሚከፍልለት ሆኖ ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ ፍጆታ የሚሆን የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚገዛ የተፈጥሮ ሰው ነው፤
11) **“የውል ሰነድ” ማለት፡-** በአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርትና አገልግሎት ግብይት

ሂደት ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ የግብይት ተዋዋይ ወገኖችመካከል በጽሁፍ የተደረገ ህጋዊ የስምምነት ሰነድ ነው፣

12) **"የግብይት ትስስር"** ማለት በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር የሚገኙ የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር የግብይት ተሳታፊዎች የግዥ እና ሽያጭ ግንኙነት የሚፈጠርበት ስርዓት ነው፤

13) **"ፈቃድ"** ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ግብይት ለማከናወን መስፈርቶችን ላሟላ ሰው የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

14) **"ፈቃድ ሰጪ አካል"** ማለት በየደረጃው ፈቃድ ለመስጠት በህግ ስልጣን የተሰጠው የመንግስት መ/ቤት ነው፤

15) **"የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት"** ማለት በአትክልት፣ ስራስር እና ፍራፍሬ ግብይት ላይ ለመሳተፍ እንዲችል ብቁ ስለመሆኑ በግብርና ሚኒስቴር የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

16) **"ጅምላ ነጋዴ"** ማለት የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርቶችን ከአምራች፣ ከህብረት ስራ ማህበራት ወይንም ከግብይት ማዕከላት በመግዛት ለላኪዎች፣ ለአቀናባሪዎች እና ቸርቻሪዎች በቀጥታ ለማስራጨት የብቃት ማረጋገጫና ህጋዊ ንግድ ፈቃድ ያለዉ ሰው ነው፤

17) **"አስመጪ"** ማለት የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርቶችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ለገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

18) **"ላኪ"** ማለት የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርቶችን ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚልክ ሰው ነው፤

19) **"አቀናባሪ"** ማለት የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርትን እሴት ጨምሮ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በማሰናዳት ለገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

20) **"ህጋዊ ወኪል"** ማለት ከአምራች ወይም የንግድ ፍቃድ ካለው የዉጪ ሀገር አስመጪ፣ ላኪ ወይም አከፋፋይ ጋር በሚገባዉ ዉል መሰረት የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ተረክቦ ጥራቱ እንደተጠበቀ ለገበያ የሚያቀርብ ሰዉ ነዉ፤

21) **"ቸርቻሪ"** ማለት የንግድ ፍቃድ ያለው - የአትክልት፣ ፍራፍሬና ስራስር ምርቶችን ከአምራች፣ ከጅምላ ነጋዴ ወይም ከዉጪ ሀገር አስመጪ ገዝቶ ጥራቱ እንደተጠበቀ በችርቻሮ ለተጠቃሚዉ የሚያቀርብ ሰዉ ነዉ፤

22) **"የእለት ፍጆታ ተጠቃሚዎች"** ማለት የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርትን

ከሻጭዎች በመግዛት ከንግድ ውጪ ለሆነ ዓላማ የሚጠቀም ሰው ማለት ነው፤

23) **“የገበያ ማዕከል”** ማለት አምራችን ማዕከል ያደረገ ለአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት መገበያያነት እንዲሆን በየደረጃው የተከለለ የመገበያያ ስፍራ ነው፤

24) **“የማሳ ላይ ግብይት”** ማለት ሻጭ በሆነ አምራች እና ገዥ በሆነ ሸማች መካከል ምርቱ በማሳው ላይ እንዳለ የሚገበያዩበት ሂደት ነው፤

25) **“የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ ማዕከል”** ማለት አምራችን ማዕከል ያደረገ ለአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት መገበያያነት በወረዳ ወይም በከተማ መስተዳድር የተከለለ መገበያያ ስፍራ ነው፤

26) **“ሁለተኛ ደረጃ ገበያ ማዕከል”** ማለት አምራቹንና ሸማቹን ማዕከል ያደረግ ለአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ማዘጋጃ፣ ማከማቻ እና መገበያያነት እንዲውል በዞን ወይም በክልል ከተሞች እና በከተማ መስተዳድር ደረጃ የተከለለ መገበያያ ስፍራ ነው፤

27) **“ተርሚናል”** ማለት በሜትሮፖሊታን እና ሪጂኦ ፖሊታን ከተሞች ከፍተኛ መጠን ያለው የአትክልት፣ ፍራፍሬና ስራስር ምርት ሽያጭ ወይም ስርጭት የሚካሄድበት የግብይት ማዕከል ነው፤

28) **“ሜትሮፖሊታን”** ማለት ጥቅጥቅ ያለ ህዝብ የሚኖርበት ከተማ እና በዙሪያው ኢንዱስትሪ፣ የንግድ አካባቢዎች፣ የትራንስፖርት አውታር፣ መሰረተ ልማት፣ መኖሪያ ቤቶች የሚጋሩበት የከተማ አስተዳደር ነው:: በውስጡም ብዙ ዋና ዋና ከተማዎች ማዘጋጃ ቤቶች፣ ሰፈሮች፣ ከተሞች፣ ወረዳዎች ያካተተ ነው፤

29) **“የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር”** ማለት፡ የአንድን ከተማ ሁለንተናዊ ልማት ከማፋጠን አንፃር አይነተኛ ማእከል በመሆን በዙሪያዉ የሚገኙትን አነስተኛ ከተሞችን ይዞ ወይም አጠቃሎ እንዲያድግ ለተመረጠ ለማናቸዉም የክልሉ ከተማ የተሰጠ መጠሪያ ነዉ፤

30) **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት እንደቅደም ተከተሉ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

31) **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

32) **“ሰው”** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

33) በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው ሁሉ ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. ዓላማ

1) በአገራችን ኢትዮጵያ በህግ የሚመራ የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት በመዘርጋት እና ተግባራዊ በማድረግ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ማረጋገጥ፤
2) የግብይት ተዋንያንን የገበያ ተሳትፎን ማሳደግ፤
3) የገበያ ተሳታፊዎች ወቅታዊ የገበያ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ፤
4) በገበያ ተሳታፊዎች መካከል የሚደረጉ ተገቢ ውድድሮችን ማዳበር፤

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀ 20 እና በሌሎች ሕጎች ለግብርና ሚኒስቴር በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ልክ በማንኛውም አትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ግብይት ሰንሰለት ውስጥ ተዋናይ በሆነ ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 5. መርሆዎች

የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ግብይት፡-

1) ህጋዊና ዘመናዊ የሆነ የግብይት ሥርዓትን ተከተሎ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፤
2) አምራቹን እና በግብይት ሂደቱ የሚሳተፉትን አካለት ፍትሀዊ ተጠቀሚነት ማረጋገጥ፤
3) ለአምራቹ እና በግብይት ሂደቱ ለሚተሳተፉ እየጨመረ የሚሄድ ምቹና ተደራሽ የሆኑ አማራጭ የገበያ ዕድሎችን ማስፋት፤
4) የአምራቾችንና የግብይት ተሳታፊዎችን የገበያ ተሳትፎ ማሳደግ፤
5) አገራዊ ለሆነ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋጾ ማበርከት፡፡

# <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የአትክልት ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ግብይት</u>

6. **<u>የግብይት አፈፃፀም</u>**

የአትክልት ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ግብይት ሊካሄድ የሚችለው፡- በምርት ማሳ፣ በመጀመሪያ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃ እና በተርሚናል ግብይት ማዕከላት ብቻ ነው፤

7. **የማሳ ላይ ግብይት**

   1) የአትክልት፣ ፍራፍሬና ስራስር ምርት ሻጭ በሆነ አምራች እና ገዥ በሆኑ፡- የእለት ፍጆታ ተጠቃሚዎች ፣ ጅምላ ነጋዴ፣ የህብረት ስራ ማህበራት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ አቅራቢ ወይም ላኪ መካከል ምርቱ በልዩ ሁኔታ በማሳው ላይ እንዳለ በቀጥታ በጽሁፍ በሚደረግ በውል ግብይት መፈጸም ይቻላል፤
   2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1) ላይ የተቀመጠው እንደተተበቀ ሆኖ የእለት ፍጆታ ተጠቃሚዎች በማሳላይ ግብይት ሲፈጽሙ በጽሁፍ የተደረገ ውል መፈጸም አይጠበቅባቸውም፤

8. **በመጀመሪያ ደረጃ ገበያ ማዕከል የሚደረግ ግብይት**

   በአምራቾች እና በአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ላኪነት፣ አቅራቢነት፣ ጅምላ ነጋዴነት የንግድ ፈቃድ በተሰጣቸው አካላት መካከል በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደሩ በተከለለ የግብይት ማዕከል ብቻ ብቻ ግብይት ማካሄድ ይቻላል።

9. **በሁለተኛ ደረጃ ገበያ ማዕከል የሚደረግ ግብይት**

   በአምራቾች፤ በአምራቾች ህብረት ስራ ማህበራት፤ ገዥ በሆኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት፣ በሕብረት ሥራ ማኅበራት፣ ቸርቻሪ፣ እንዲሁም በአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ላኪነት፣ አቅራቢነት፣ ጅምላ ነጋዴነት፣ በአቀነባባሪነት የንግድ ፈቃድ በተሰጣቸው አካላት መካከል ብቻ በዞን ወይም በክልል ከተሞች እና በከተማ መስተዳድር በተከለለ የግብይት ማዕከል በጽሁፈ በተደረገ ውል ግብይት ሊካሔድ ይችላል።

10. **በተርሚናል የግብይት ማዕከል የሚደረግ ግብይት፡-**

    በአትክልት ፍራፍሬና ስራስር አምራች፣ በአምራች ህብረት ስራ ማህበራት፤ በሸማች፣

ህብረትስራ ማህበራት፤ በአቅራቢ እና ጅምላ ነጋዴ ሻጭነት፣ በላኪ እንዲሁም በአቀናባሪዎች መካከል በጽሁፍ በተደረገ ውል ግብይት መፈጸም ይቻላል፡፡

11. **የግብይት ማዕከላት የግብይት ቀንና ሰዓት አወሳሰን፡-**

የአትክልት፣ ፍራፍሬና ስራስር ምርቶች ከሌሎች ምርቶች በተለየ ሁኔታ በቀላሉ የሚበላሹ መሆናቸዉን፣ የሴቶችን ተደራራቢ የስራ ጫና እና ሌሎች አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በየደረጃው በወረዳ ወይም በከተማ መስተዳድር፣ በዞን ወይም በክልል ከተሞች፣ በከተማ መስተዳድር እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ይወሰናል፡፡

12. **የአትክልት ፍራፍሬና ስራስር ምርቶችን ስለማጓጓዝ**

በዝቅተኛ ደረጃ አምርተው ወደ ገበያ ከሚያወጡ አርሶ አደሮችና ከዕለት ፍጆታ ተጠቃሚዎች በስተቀር ማንኛውም የግብይተ ተሳታፊ አትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ማጓጓዝ የሚችሉት ከዚህ በታች በተዘረዘረው አግባብ መሆን አለበት፡-

1) የአትክልት፣ ፍራፍሬና ስራስር ምርቶች በመጠን እና በአይነት ተለይተው በአንድ ላይ በማይቀላቀሉበት ሁኔታ፤
2) የምርቱ መጠን ወይንም ይዘቱ፣ ጣዕሙ፣ ቀለሙ፣ እርጥበቱና ጥራቱ እንደተጠበቀ ከቦታ ወደ ቦታ ለማጓጓዝ በሚረዳ ከፕላስቲክ፣ ከእንጨት፣ ከቀርቀሀ ወይም ከሸንበቆ እና ከሌሎች ቁሳቁስ አየርር እነደልቡ ማዘዋወር እንዲችል ተደርጎ በተሰራ ሳጥን፤
3) በአቅራቢ ወይም በአምራች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ገበያ ማእከላት፤ ተርሚናል ገበያዎችና ወደ ውጪ ገበያ የሚጓጓዝ የአትክልት ፍራፍሬና ስራስር ምርት ሲጫን በሚመለከተዉ የጥራት ተቆጣጣሪ በጥራትና በዓይነት ተለይቶ ደረጃዉን በጠበቀ የትራንስፖርት አገልግሎት መጓጓዝ አለበት፤
4) የምርት ማጓጓዣ ዕቃው ለዚሁ አገልግሎት ብቻ የተዘጋጀና ለሌሎች አገልግሎቶች ጥቅም ላይ ያልዋለ መሆን አለበት፤
5) ምርት የሚጓጓዝበት ማጓጓዣ የምርቱን ጥራት በቀላሉ ሊያበላሹ ከሚችሉ እንደ ቆዳና ሌጦ፣ ነዳጅ፣ ኬሚካል ከመሳሰሉ ቁሳቁሾች የፀዳና ከምርቱ ጋር የሚፃረር ባእድ ነገር በደባልነት ያልጫነ መሆን አለበት፤
6) ምርት የሚጓጓዝበት ማጓጓዣ እርጥበት፤ ፀሀይና አቧራ በማያስገባ ሁኔታ ተሸፍኖ መጓጓዝ አለበት፤
7) ወደ ዉጪ የሚላኩ ምርቶች የሚጓጓዝበት የትራንስፖርት አይነት የምርቱን ጥራትና ደህንነት በሚያስጠብቅ መልኩ መሆን አለበት፤

8) አርሶና አርብቶ አደር ለሆኑ የአትክልት፣ ፍራፍሬና ስራስር ምርት ወደ ገበያ ሲያጓጉዙ በግብርና ባለሙያዎች ምክረ-ሀሳብ መሰረት መሆን አለበት።

**13. የአትክልት ፍራፍሬና ስራስር ምርት ጥራት ቁጥጥር**

1) በመጀመሪያ ደረጃ የአትክልት ፍራፍሬና ስራስር ምርት ግብይት ማዕከላት ግብይት የሚፈጸምባቸው የአትክልት ፍራፍሬና ስራስር ምርቶች ጥራታቸው በገበያ ማዕከሉ በሚገኙ የአትክልት ፍራፍሬና ስራስር የጥራትና ቁጥጥር እንዲከታተል በህግ ስልጣን በተሰጠው ተቋም እንዲረጋገጥ ይደረጋል፤

2) ወደ ውጭ አገር የሚላኩ የአትክልት ፍራፍሬና ስራስር ምርቶች ደረጃውን በጠበቀ የኳራታይን ጣቢያ በጥራት አረጋጋጭ ተቋም ቁጥጥር ተደርጎበት እንዲወጣ ይደረጋል።

# ክፍል ሶስት

# <u>የግብይት ማዕከላት አከላለል እና አስተዳደር</u>

## <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

## <u>የግብይት ማዕከላት አከላለል</u>

14. የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል ከሚመለከተው የወረዳ የመንግስት ተቋማት እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ የግብይት ማዕከላትን የዞንና የክልል የመንግስት ተቋማት፣ ማህበረሰቡን እና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር አትክልት፣ ፍራፍሬና ስራሰር ምርት አቅርቦት፣ የግብይት ተዋንያኖችን እና የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት በማስገባት የሚከለል ግብይት ማዕከላት ብዛትና ስርጭት በመወሰን እንዲከለል ይደረጋል፤

በመሆኑም የምርት ግብይት ማዕከላትን ብዛትና ስርጭት ሲወስን እና ሲከለል ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ዋናዋና ጉዳዮች፤-

1) ለአምራቾችና ለግብይቱ ተሳታፊዎች ያላቸውን ቀረቤታ እና አማካይነት፤
2) ተሽከርካሪን ለማስገባትና ለማስወጣት ያላቸውን አመቺነት፤
3) ለአትክልት ፍራፍሬና ስራስር ምርቶች የግብይት አገልግሎት ለመስጠት ያላቸውን አመቺነት፤ እና

4) ከትምህርት ቤቶች፣ ከጤና፣ ከእምነት እና ከሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ተፅዕኖ በማይፈጥር እና ካለው አካባቢ ነባራዊ ሁኔታን ከግምት በማስገባ መከልል አለበት፡፡

15. ለግብይት የሚከለሉ ማዕከላት እነደየ ደረጃው እና የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የሚከተሉትን መሰረተ ልማቶች ሊያሟሉ ይገባል፡-

1) ለሚፈለገው ግብይት በቂ የሆነ የቦታ ስፋት፤
2) አቅም በፈቀደ መጠን በአካባቢዉ የሚገኝን ቁሳቁስን በመጠቀም ለግብይቱ ተሳታፊዎች እና ለማዕከሉ ሰራተኞች የሚሆን የመገበያያ መጠለያ ቦታ፤
3) ደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ፤ የአትክልት ፍራፍሬና ስራስር ተረፈ ምርት ማስወገጃ ስፍራ፤
4) ለግብይቱ ተሳታፊዎች እና ለማዕከሉ ሰራተኞች የጋራ መገልገያ የሚሆን፡- ሴቶችንና አካል ጉዳተኞችንና ሌሎች ልዩ ፍላጎቲችን ታሰቢ ያደረገ የመፀዳጃ ቤት፣
5) ተሽከርካሪን ለማስገባትና ለማስወጣት አመቺ የሆነ የመኪና ማቆሚያ፣ መጫኛና ማውረጃ ቦታ፤
6) የእለቱ የገበያ መረጃ መለጠፊያ ሰሌዳ እና ሌሎች ጠቃሚ የሆኑ መሰረተልማቶች፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የግብይት ማዕከላት አስተዳደር

16. የግብይት ማዕከላት አደረጃጀት፣ አሠራር እና አስተዳደርን በተመለከተ እንደየ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ግንዛቤ በማስገባት የግብይት ማዕከላትን አስተዳደር፣ አሰራር ስርዓት ሕግ በማውጣት ይወሰናል፤

17. የግብይት ማዕከላቱን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው አካል የግብይት ቦታው በአትክልት፣ ፍራፍሬና ስራስር ምርቶች ጥራት ላይ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ ሁኔታዎች ነፃ እንዲሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር መስራት አለበት፡፡

# ክፍል አራት

## <u>ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና የግብይት ተዋንያን መብትና ግዴታዎች</u>

### ንዑስ ክፍል አንድ

### <u>ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት</u>

**18. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያስችሉ ሁኔታዎች**

1) ከአምራች በስተቀር ማንኛውም የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ግብይት ተዋንያን - የንግድ ፈቃድ ከተሰጠው በኋላ በሚመለከተው ተቋም የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፤

2) የሀገር ውስጥ የግብይት ተዋንያን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ቢያንስ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፦

   ሀ) ቢያንስ አንድ ደረጃውን የጠበቀ በዘመኑ የተመረመረ ሚዛን ፤

   ለ) ቀዝቃዛና አየር እንደልብ ማዘዋወር የሚችል በቂ የግብይት ቦታ፤

   ሐ) እንደሚካሄደው የግብይት መጠን ወይም ደረጃ ስፋቱ በቂ የሆነ ቀዝቃዛና አየር እንደልብ ማዘዋወር የሚችል የግብይት ቦታ፤

   መ) ወለሉ ከሲሚንቶ ወይም ከእንጨት ውጤቶች የተሰራ፤

   ሠ) የግድግዳው ከፍታና ወለል የምርት ክምችት መጠንን ታሳቢ ያደረገ፤

   ረ) ምርቱን ከቦታ ወደ ቦታ ለማጓጓዝ የሚረዳ ከፕላስቲክ ወይም ከጣውላ የተሰራ ክፍት የፍራፍሬ ሳጥን፤

   ሰ) በየእለቱ የምርት አቅርቦት፣ ስርጭት፣ ጥራት ደረጃና ዋጋ መመዝገቢያ መዝገብ፤

   ሸ) በቂና ንጽህናው የተጠበቀ ለተጠቃሚዎች ለመያዣና ለማጓጓዣነት የሚያገለግል ከጨርቅ የተሰራ ኪስ ያለዉ ከረጢት ማዘጋጀት የሚችል፤

   ቀ) ንጽህናው የተጠበቀና የማይዝግ ለግብይት የሚጠቀምበት ቁሳቁስ፤

   በ) ለስራው የሚያስፈልግ በቂ የሰው ኃይል መሟላት አለበት።

3) **ምርት ወደ ውጪ ላኪ - ወደ ወጪ ለሚላኩ ምርቶች - የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ቢያንስ የሚከተሉትን** ማሟላት አለበት፦

   ሀ) ለወጪ ገበያ የሚሆነውን የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ጥራት ደረጃ ለማስጠበቅ የሚያስችል ማቀዝቀዣ፣ መጋዘን፣ ማጓጓዣ እና ማሸጊያ ቁሳቁስ፤

ለ) ደረጃውን የጠበቀ በዘመኑ የተመረመረ ቢያንስ ሁለት የምድር ድጂታል ሚዛን፤

ሐ) በየእለቱ የምርት አቅርቦት፣ ስርጭት፣ ጥራት ደረጃና ዋጋ መመዝገቢያ መዝገብ፤

መ) የምርቱን የጥራት ደረጃ የሚለይ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያለው ባለሙያ፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## <u>የግብይት ተዋንያኑ መብትና ግዴታ</u>

**19. የግብይት ተዋንያን መብት**

**ማንኛውም በአትክልት፣ ፍራፍሬና ስራስር ምርት ግብይት ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ቀጥለው የተዘረዘሩት መብቶች አሉት፡-**

1) በሚመለከተው አካል በተፈቀዱና ዕውቅና በተሰጣቸው የግብይት ማዕከላት የመግዛትና የመሸጥ መብት፤
2) ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል በህግ አግባብ ስልጣን በተሰጠው ተቋም የሚያወጣዉን የቴክኒክ መስፈርት መሠረት አደርጎ የሚሰጠውን የንግድ ፈቃድ የማግኘት መብት፤
3) በዚህ መመሪያ በተደነገገው የቴክኒክ እና የግብይት አሠራር መሠረት ተጠቃሚ የመሆን መብት፤
4) የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ለውጪ ወይም ለሀገር ውስጥ ገበያ ከመጫኑ በፊት የምርት ጥራት መስፈርት በሚመለከተው ተቋም እንዲረጋገጥለት ሲጠይቅ አገልግሎት የማግኘት፤
5) ግብይት ከተፈፀመበት አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ለማጓጓዝ አግባብ ካለዉ አካል መሸኛ ደብዳቤ እንዲፃፍለት ሲጠይቅ መሸኛ የማግኘት፤
6) አልሚ ባለሃብት ከሆነ ከአመራቾች ጋር የግብይት ትስስር የመፍጠርና ምርት የመግዛት መብት አለው፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## <u>የግብይት ተዋንያን ግዴታ</u>

**20. የአምራች ግዴታዎች፡-**

**ማንኛውም የአትክልትና ፍራፍሬ አምራች፡-**

1) ያመረተውን ምርት ጥራቱ ሳያጓድል በማንኛውም የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ግብይት በተፈቀደለት ቦታ ብቻ የመሸጥ፤

2) የመሬት ማረጋገጫ ይዞታ ደብተር ካላዉ አርሶ አደርና ከአርሶ አድር ተከራይተው ከሚያመርቱ በስተቀር ከሚመለከተዉ የመንግስት አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫና የኢንቨስትመንት ፈቃድ የመያዝ፤

3) ያመረተውን ምርት በቀጥታ ወደ ዉጪ ሲልክ የሃገሪቱን የንግድ ፍቃድ እና የጥራት ደረጃ የማሟላት፤

4) በራሱ ወይም በአከባቢው ወይም በሃገሪቱ የሚታወቅ አስገዳጅ ሁኔታ ካልገጠመው በስተቀር ያመረተዉን ምርት በወቅቱ የመሸጥ፣

5) ለጥራት ምርመራ አገልግሎት የሚውል በተለያየ የግብይት ደረጃ ያለውን ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና የመስጠት ወይም የማቅረብ፤

6) ማንኛውም አምራች ምርቱ ትክክለኛ የብስለት ደረጃ ላይ ያልደረሰ ምርት ለገበያ ያለማቅረብ፣

7) ምርቱን ደረጃውን በጠበቀና ከኬሚካል ንክኪ በጸዳ መጋዘን ማከማቸትና በፍጥነት ሳይበላሽ ለተጠቃሚው እንዲደርስ ማድረግ፤

8) ለገበያ የቀረበ ምርት በተቆጣጣሪ ምርመራ ተደርጎበት እንዲወገድ የተሰጠውን ውሳኔ የማክበርና የመፈፀም፣

9) ይህንን መመሪያ ተከትሎ የሚወጡ ተጨማሪ የቴክኒክ እና የአሰራር ሥርዓቶችን የማክበርና የመፈፀም ግዴታ አለበት፣

21. <u>የጅምላ ነጋዴ ግዴታ፡</u>

**ማንኛውም የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ነጋዴ ፡-**

1) በተወሰነለት የገበያ ማእከላት ጥራቱን የጠበቀ ምርት መግዛትና የመሸጥ፤

2) አግባብ ካለዉ የመንግስት አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የንግድ ፍቃድ የመያዝ፤

3) ደረጃውን የጠበቀና በዘመኑ የተመረመረ ዲጂታል የምድር ሚዛን የመያዝ፤

4) የተበላሸ ምርት ከጤነኛው ጋር ቀላቅሎ ያለመሸጥ፤

5) የተበላሸን ምርት የሰውንና የእንስሳትን ጤና በማይጎዳ ሁኔታ በአግባቡ ማስወገድ፤

6) ደረጃዉን የጠበቀ ምርት ማቆያ ወይንም ማከማቻ መጋዘን የማዘጋጀት፤

7) የምርት ማቆያ መጋዘን ለየአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርቶች ማቆያነት ብቻ መጠቀም፤

8) የምርት ሽያጭ ላይ የሚሰማሩ ሰራተኞች ንጽህናቸው የተጠበቀ የደንብ ልብስ የመጠቀም፤
9) የየዕለቱን ምርት ግዥና ሽያጭ መጠን፣ ደረጃና የዋጋ ዝርዝር እና ለግብይት ስርዓቱ ጠቃሚ የሆኑ ማንኛቸውንም መረጃ መዝግቦ የመያዝና በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሲጠየቅ የማሳየት፣
10) ከግብይት ማዕከል ወይም ከማሳ ላይ የገዛውን ምርት ከማጓጓዙ በፊት አግባብ ካለው አካል መሸኛ የማግኘት፤ ሲጠየቅ የማሳየት፤
11) ለምርት ጥራት ምርመራ አገልግሎት የሚውል ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና የመስጠት ወይም የማቅረብ፤
12) ይህንን መመሪያ ተከትሎ የሚወጡ ተጨማሪ የቴክኒክ እና የአሰራር ሥርዓቶችን የማክበርና የመፈፀም ግዴታ አለበት።

22. **<u>የላኪ መብትና ግዴታዎች</u>**

1) አግባብ ካለዉ የመንግስት አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የንግድ ፍቃድ የመያዝ፤
2) ከተፈቀደለት የግብይት ማዕከል ወይም ስፍራ መግዛት፤
3) ወደ ዉጪ የሚላከዉን ምርት በገዥው ሀገር የጥራት ደረጃ እና የቴክኒክ መስፈርት መሰረት አዘጋጅቶ የመላክ፤
4) የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ለዉጪ ገበያ ለማቅረብ የውል ስምምነት ሲፈጸም ለባለሥልጣኑ በሶስት (3) የሥራ ቀናት ውስጥ የማሳወቅ፤
5) ከህጋዊ ጅምላ ነጋዴ ወይም አምራች ወይም ማኅበራት የገዛውን ምርት ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ አዘጋጅቶ በወቅቱ የመላክ፣
6) ወደ ውጪ የሚላከውን ምርት የጥራት ደረጃ እና የደህንነት ምርመራ (ኳራንቲን) የማስደረግና የምርመራ ውጤት የመያዝ፤
7) ለጥራት ምርመራ አገልግሎት የሚውል በተለያየ የግብይት ደረጃ ያለው ምርት ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና የመስጠት ወይም የማቅረብ፤
8) ይህንን መመሪያ ተከትሎ የሚወጡ ተጨማሪ የቴክኒክ እና የአሰራር ሥርዓቶችን የማክበርና የመፈፀም ግዴታ አለበት።

23. **<u>ቸርቻሪ ነጋዴ ግዴታዎች</u>**

ማንኛዉም የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ቸርቻሪ ነጋዴ፡-

1) የገዛውን ምርት ለተጠቃሚ በጥራት የማቅረብ፣
2) ከሚመለከተው የመንግስት አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የችርቻሮ ንግድ ፈቃድ መያዝ፣
3) ደረጃውን የጠበቀና በዘመኑ የተመረመረ ዲጂታል ሚዛን ሊኖረው ይገባል፤
4) ለተጠቃሚ የሚያቀርበዉን ምርት ከአምራች፣ ህጋዊ ፍቃድ ከተሰጠው አካል የመግዛት፤
5) አስገዳጅ ሁኔታ ካልገጠመው በስተቀር የችርቻሮ የመሸጫ ቦታውን አለመዝጋት፤
6) በማንኛውም ጊዜና ወቅት የስራ ቦታው ለሸማች ህብረተሰብ ግልጽ በሆነ መንገድ
7) የየዕለቱን የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ የመለጠፍ፤
8) ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚያቀርበው ምርት ጥራቱንና ደህንነቱን የመጠበቅ፤

ግዴታ አለበት፡፡

24.<u>የአቀናባሪ ግዴታዎች</u>

**ማንኛዉም የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት አቀነባባሪ፡-**

1) የአትክልት፣ ስራስርና ፍራፍሬ አቀናባሪነት ህጋዊ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትና የማቀናበር ንግድ ፈቃድ የመያዝ፣
2) ከግብይት ስፍራ የመግዛትና ወይንም በቀጥታ ከአምራች አካባቢዎች ምርት ወደ ማቀነባባሪያ ኢንዱስትሪ ሲያጓጉዝ መሸኛ ሰነድ የመያዝ፤
3) የአትክልት፣ ስራስርና ፍራፍሬ ምርት ሻጩ ጋር የገባውን ዉል በዉሉ የጊዜ ገደብ ውስጥ የመፈጸም፤
4) ለጥራት ምርመራ አገልግሎት የሚውል በተለያየ የግብይት ደረጃ ያለው ምርት ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና የመስጠት ወይም የማቅረብ፤
5) ይህንን መመሪያ ተከትሎ የሚወጡ ተጨማሪ የቴክኒክ እና የአሰራር ሥርዓቶችን የማክበርና የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡

# ክፍል አምስት

## ከዚህ መመሪያ ጋር ግንኙነት ያላቸው ተቋሞች የስራ ድርሻና ኃላፊነት

አትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስርና ምርት ግብይትን ለመደገፍ የገበያ ስርዓትን ከማጠናከር አንጻር የሚከተሉት በዋናነት ድርሻ ይኖረቸዋል፡፡

25. **ግብርና ሚኒስቴር**

1) ግብርና ሚኒስቴር የአትክልት፣ **ስራስርና** ፍራፍሬ ምርት ግብይት ስራን በበላይነት በመደገፍ የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባራትም ያከናውናል: -
   ሀ) ምርት ግብይት አፈጻጸም አስመልክቶ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ስራውን ይመራል፣ ያስተባብራል ይደግፋል እንዲሁም በቅንጅት እንዲመራ ያደርጋል፤
   ለ) በዘርፉ ለሚሰማሩ ተዋንያኖችና አጋር ባለድርሻ አካላት በየጊዜው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ያከናውናል፤
   ሐ) የምርት ግብይት ተዋንያን የገበያ የትስስር መድረክ እንዲፈጠር ያመቻቻል፤
   መ) የምርት ግብይት ተዋንያን የቴክኒክ፣ የሙያ ስልጠና፣ ድጋፍ እና ክትትል ይሰጣል፤
   ረ) የግብይት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤
   ሰ) የግብይት አፈጻጸም ከመደገፍ አንጻር የምርት ማጓጓዝ ሎጀስቲክስ አቅርቦት፣ ሌሎች ችግሮችን ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ጋር በመቀናጀት እንዲፈታ ያደርጋል፤
   ሸ) የግብይት አፈጻጸም ጋር የተያያዙ የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ለሚመለከተው አካል ይልካል፤ (በፆታና እድሜ የተለ የተለየ መረጃ)
   ቀ) ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ድጋፍና እገዛ ያደርጋል።

26. **ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር**

1) በአትክልት፣ **ስራስርና** ፍራፍሬ ምርቶች ግብይት ስራ ለመሰማራት ለሚፈልጉ አካላት የንግድ ፈቃድ ይሰጣል፤
2) በዘርፉ የሚሰማሩ አካላት የቴክኒክና የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤
3) ኤክስፖርት የገበያ መዳረሻዎችን ከማስፋት አንጻር ዓለም አቀፍ ኤክስፖዎችን፣ ባዛሮችን፣ ኤግዚቢሽኖችንና ሲምፖዚየሞችን ከሚመለከታቸውጋር በማዘጋጀት የማስተዋወቅና የትስስር ስራ ያከናውናል፤

4) ከዘርፉ ጋር በተያያዘ የውጭ ገበያ ለማስፋት ኤክስፖርተሮች የሚጠይቁትን የምርት የናሙና ለመላክ ድጋፍ ይሰጣል፤
5) የወጭ ንግድ አፈጻጸም የተሻለ ውጤት እንዲመዘገብ ያግዛል፣ ያበረታታል፣ ዕውቅና ይሰጣል፤
6) ወደ ዉጪ የሚላኩና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ጥራትና ስታንዳርድ ቁጥጥር ያደርጋል፤
7) የገበያ መሰረተ ልማት እንዲሟላ ያደርጋል፣ ወቅታዊ የገበያ መረጃ ተደራሽ ያደርጋል፤
8) ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ድጋፍ ያደርጋል።

27.**ገቢዎች ሚኒስቴር**

1) በአትክልት፣ **ስራስርና** ፍራፍሬ ምርቶች ግብይት የተሰማሩ አካላት ከአነስተኛ አምራቾች የምርት ግብይት ሲፈጽሙ ደረሰኝ ማቅረብ የማይችሉትን በተቋሙ በኩል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በልዩ ሁኔታ የሚስተናገዱበት ሁኔታ ያመቻቻል፤
2) በዘርፉ የተሰማሩ ላኪዎችን ቅድሚያ ተሰጥቶት የሚስተናገዱበት አፋጣኝ የሆነ ሥርዓ ትእንዲተገበር ያመቻቻል፣ ይደግፋል፤
3) ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ድጋፍ ያደርጋል።

28.**ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር**

1) ኤክስፖርት የሚታየውን የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አቅርቦት ችግሮች ለመፍታት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመቀናጀት ድጋፍ ያደርጋል፤
2) ኤክስፖርት ምርቶች የሚያገለግሉ የትራንስፖርትና የሎጀስቲክስ ፋሲሊቲዎች አማራጭ መንገዶችን በማመቻቸት የዘርፉን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ከቀረጥ ነጻ እንዲገባ ቅድመ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
3) ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ድጋፍ ያደርጋል።

29. **የስራና ክህሎት ሚኒስቴር**

1) በዘርፉ የተሰማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስተሪዎች ጋር የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ተቀናጅቶ ይሰራል፤

2) የዕሴት ሰንሰለትን መሰረት በማድረግ ለሀገር ውስጥ ገበያ በስፋት ሊመረቱ የሚችሉ የገበያ ዕድል እና የሚያስፈልጉ ድጋፎች ዝርዝር የገበያ ፕሮፋይል ያዘጋጃል፤
3) በሚዘጋጁ የንግድ ትርኢትና ባዛር በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት የገበያ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እንዲቻል አገር ዓቀፍ ተሞክሮን መሰረት ያደረገ የንግድ ትርኢትና ባዛር ያዘጋጃል፤
4) በአትክልት፣ **ስራስርና** ፍራፍሬ ምርት አገር ውስጥ ገበያ እንዲያገኙ መከናወን ያለባቸውን ዝርዝር ተገባራት በመለየት የሚመለከታቸው አካላት የሚጠበቅባቸው እንዲወጡ የማስተባበር ስራ ያከናውናል፤
5) ስራ ፈላጊ ሴቶች፣ ወጣቶችና ስራ መስራት የሚችሉ አካል ጉዳተኞች በዚህ ዘርፍ እንዲሰማሩ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ያመቻቻል፤
6) በዘርፉ ፍላጎት ያላቸዉን ኢንተርፕራይዞች አደራጅቶ ወደ ስራ ያስገባል፡፡

## 30. የኢትዮጵያ ህብረት ስራ ኮሚሽን

1) የግንዛቤ ማስጨበጫና ሁለንተናዊ አቅም ግንባታ ስራዎችን ይሰራል አተገባበሩንም ይከታተላል፤
2) የምርት ግብይት ማሳለጥ እንዲቻል የመረጃ ልውውጥ ሁኔታን ያመቻቻል፣ ያደራጃል፣ ድጋፍ ይሰጣለል፤
3) ምርት ባለበት አካባቢ የተደራጁ ኅብረት ስራ ማህበራት ከሌሉ ያደራጃል፣ ነባር ኅብረት ስራ ማህበራትን ያጠናክራል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
4) ሴቶች፣ ወጣቶችና አካል ጉዳኞችን በመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት በማደራጀት በአትክልት፣ስራስርና ፍራፍሬ ምርት ግብይት ሂደት ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያመቻቻል፤
5) ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ድጋፍና እገዛ ያደርጋል፡፡

## 31. ግብርና ባለስልጣን

1) የአትክልት፣ **ስራስርና** ፍራፍሬ ምርቶች ግብይት ተዋናዮችን የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ግብይት የብቃት ሰርተፍኬት እንዲያገኙ ይሰጣል፤

2) ኤክስፖርት ምርቶችን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ የተለያዩ የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገቡ ፈቃድ ይሰጣል፤
3) ወደውጪ ለሚላኩ ምርቶች የፋይቶሳኒታሪ ቁጥጥር በማድረግ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡
4) ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ድጋፍ ያደርጋል፣

## 32.ጉምሩክ ኮሚሽን

1) የምርት ላኪዎች ግብይት እንዲሳለጡ የሚስተናገድበት አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤
2) በባህርያቸው በቀላሉ የሚበላሹና ለጉዳት የሚጋለጡ ምርቶችን የቅድሚያ አገልግሎት አግኝተው የሚስተናገዱበት ምቹ ሁኔታ ያመቻቻል፤
3) ከውጪ የሚገቡ ለላኪ ግብይት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች የሚገቡበትን መንገድ ያመቻቻል፤
4) ለምርት ግብይት የኤክስፖርት ፎርማሊቲዎችን እንዲያሟላ ቅድመ ሁኔታ ያመቻቻል፤
5) የኤክስፖርት መረጃ በየወሩ ለሚስትሩ እንዲደርስ **ያደርጋል፡፡**
6) ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ድጋፍ ያደርጋል፤

## 33.ኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

1) የአትክልት፣ **ስራስርና** ፍራፍሬ ምርቶች ግብይት በአምራችነት፣ በላኪነት ለመሰማራት ለሚፈልጉ- ለውጭና ለሃገር ውስጥ ባለሃብቶች የማስተዋወቅ ሥራ ይሰራል፤
2) በዘርፉ ለሚሰማሩ የግብይት ተዋንያን የኢንቨስትመንት ፈቃድ በልዩ ሁኔታ የሚያገኙበትን መንገድያመቻቻል፤
3) በአምራችነት፣ በላኪነት ወይም በአቀናባሪነት ለሚሰማሩ አካላት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
4) በአትክልት፣ **ስራስርና** ፍራፍሬ ምርቶች ግብይት የተሰማሩ ሴት ኢንቨስተሮችን የማረታቻ ድጋፎችን፣ የኢቨስትመንት ማስፋፊያ መሬት፣ የብድር አቅርቦት እንዲያገኙና የገበያ ትስስር ያመቻቻል፤
5) ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራትን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

### 34. ብሔራዊ ባንክ

በላኪነት ለተሰማሩ የግብይት ተዋነያት የውጭ ምንዛሬ ቅድሚያ አገልግሎት እንዲያገኙ ያመቻቻል፤

1) በላኪነት ለተሰማሩ የግብይት ተዋነያት ከኤክስፖርት ምርቶች የተገኘ የውጭ ምንዛሬ ወቅቱን ጠብቆ በአግባቡ ስለመግባቱ ወይም ተመላሽ ስለመደረጉ (ሪፓትሬሽን) ይከታተላል፣ መረጃ በማደራጀት ለሚመለከታቸው ተቋማት ይልካል፤
2) የኤክስፖርት ፐርሚት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይከታተላል፤
3) ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራትን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

### 35. የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን

1) ምርቱ ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃቸውን ጠብቆ እንዲጓጓዝና በገበያው ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲቀርብ ተገቢዉን አገልግሎት ይሰጣል፤
2) ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራትን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

### 36. የኢትዮጵያ አየር መንገድ

1) የምርት መላኪያ ኤርዌይ ቢል ያዘጋጃል እንዲሁም የምርት መላኪያ ኢንሀውስና ማስተር ኤርዌይ ቢሎች እንደ አስፈላጊነቱ ያዘጋጃል፤
2) የምርት ግብይት የተሳለጠ እንዲሆን ይህን ዘርፍ ከመደገፍና ማበረታታት አንጻር የምርት መለኪያ ወጪን በሚመለከት ዘርፉን ታሳቢ ያደረገ አገልግሎት ይሰጣል፤
3) በቀላሉ የመበላሸት ባህሪ ላላቸው ምርቶች በቂ የካርጎ ቦታና የቅድሚያ በረራ የማመቻቸት፣የማገዝና የመደገፍ አገልግሎት ይሰጣል፤
4) በቀላሉ የሚበላሹ ስለሆኑ አለም አቀፍ እስታንዳሩዱን በቂ ማካማቻ መጋዘን ያመቻቻል፤
5) ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

### 37. የንግድ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት

1) የወጭ ንግድ እንዲስፋፋ (የገበያ መዳረሻዎን በማፈላለግ፣ የምርት ማሳያ ኤግዚቢሽኖች በማዘጋጀት) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይደግፋል፣ ያግዛል፣
2) የግብይት አፈጻጸም ሂደት በዘርፉ ተዋንያን መካከል አለመግባባትና ክርክር ሲፈጠር ከሚመለከተው አካል ጋር በጋራ ችግሮችን ይፈታል፤
3) የዘርፍ ችግሮች ላይ ጥናትና ምርምሮችን በጋራ በማካሄድ አማራጭ ምክረ ሃሳቦችን በማቅረብ ረገድ ስራዎችን ያከናውናል፤
4) የአቅም ግንባታ ስራዎችን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር በጋራ በመሆን የከናውናል፤
5) ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 38. የአትክልት፣ ስራስርና ፍራፍሬ ምርት ግብይት ተቆጣጣሪ ስልጣንና ተግባር

1) አግባብ ባለው አካል በተፈቀደ የንግድ ቦታ ብቃት ማረጋገጫ በተሰጣቸው ምርት ግብይት ተዋንያን መካከል ሕጋዊ ግብይት መፈጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡
2) ወደ ማንኛውም የአትክልት፣ ስራስርና ፍራፍሬ ምርት ማከማቻ ስፍራ በሥራ ሰዓት መግባትና የግዥ፣ ክምችትና ሽያጭ ቁጥጥር ያደርጋል፤
3) የአትክልት፣ ስራስርና ፍራፍሬ ምርት ጅምላና ችርቻሮ ንግድን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
4) ወደ ወጪ የሚደረግ ሽያጭ ኮንትራት አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
5) የግብይት አሰራር ጉድለት በታየባቸው የግብይት ተሳታፊዎች ተገቢዎን እርምት እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
6) የአትክልት፣ ስራስርና ፍራፍሬ ምርት ግብይት ቁጥጥርን በሚመለከት መረጃ ያደራጃል ለሚመለከተው የበላይ አካል ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፤
7) ግብይትን አስመልክቶ የተከለከሉ ተግባራት ተብሎ በተገለጸው አንቀጽ ሥር የተቀመጡትን ክልከላዎች መተግበራቸውን ይቆጣጠራ፡፡

## 39.የምግብ እና መድሐኒት አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር

1) ማንኛውም የምግብ አምራች፣ አስመጪ ወይም አዘጋጅ ለምግብ ማምረት አገልግሎት የሚውል ጥሬ ዕቃ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፤

2) ማንኛውም የታሸገ ምግብ አምራች ድርጅት በሚያመርተው ምግብ ዓይነት፣ ይዘትና የአመራረት ሂደት ላይ ለውጥ ያደረገ እንደሆነ ለአስፈጻሚው አካል ማሳቀወቅ አለበት፤
3) የየአትክልት፣ ስራስርና ፍራፍሬ ማቀነባበሪያ ኢንዱስተሪዎች በመገኘት የምርት ጥራትን ይከታተላልና ይቆጣጠራል፤
4) ወቅታዊ በሆኑ ጥራት ቁጥጥር አሰራሮች ላይ የተጠቃሚዎችን ግንዛቤን፣ ዕውቀትንና ክህሎትን ለማሳደግ የሚረዱ ማንዋሎችን፣ በራሪ ጽሁፎች፣ ፖስተሮችና መጽሄቶች ያዘጋጃል፣ ሥልጠና ይሰጣል፤
5) ወደ ማንኛውም መጋዘን፣ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ወይም የአገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቦታ ከፍትህ አካላት ጋር በመተባበር በሥራ ሰዓት ለመግባትና የየአትክልት፣ ስራስርና ፍራፍሬ ናሙና ወስዶ ማጣራት፤
6) የአትክልት፣ ስራስርና ፍራፍሬ ማዘጋጃ እና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የምርት አከመቻቸትና አያያዝን በተመለከተ ጥራቱ እንዲጠበቅ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤
7) በየአትክልት፣ ስራስርና ፍራፍሬ ጥራት ቁጥጥር ሥራዎች ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት ወቅታዊ መረጃ በማሰባሰብ መፍትሄ እንዲሰጥበት ሀሳብ ያቀርባል፤
8) የየአትክልት፣ ስራስርና ፍራፍሬ በተፈቀደና በንፁህ መያዣ መደረጉን፣ የሚጭነው ተሽከርካሪ ከመጫኑ በፊት የስፖንዳውን ንፅህና፣ ንጹህና ዝናብ የማያስገባ ሸራ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤
9) የተዘጋጀና የተላከ አትክልት፣ ስራስርና ፍራፍሬ ምርት መጠን መረጃ በጥራት ደረጃ ለይቶ ያዘጋጃል፣ ለሚመለከታቸው እንዲተላለፍ ያደርጋል፤
10) የጥራት ጉድለት በታየባቸው የግብይት ተሳታፊዎች ተገቢውን እርምት እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፤

## 40. የክልልና ከተማ አስተዳደር ተግባርና ሀላፊነት

የአትክልት፣ ስራስርና ፍራፍሬ ምርት ግብይት አጠቃላይ ሂደት ይህን መመሪያ መጠቀም ወይም ይህንን መመሪያ መሰረት በማድረግ ከራሳቸው ተጨባች ሁኔታ በመነሳት መመሪያ አዘጋጅተው መጠቀም ይችላሉ።

## 41. የሆርቲካልቸር አምራቾችና ላኪዎች ማህበር

1) ምርት ግብይት አፈጻጸም ዙሪያ የሚያጋጥሙ ችግሮች አፈታት ዙሪያ ከሚመለከታቸው

ተቋማት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፤

2) በዓለም ቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ የማማከር፣ የሙያና ቴክኒክ እገዛና የስልጠና ድጋፎች ያከናውናል፤
3) በዘርፉ ችግሮች ዙሪያ ጥናት ያደርጋል፣ ለፖሊሲ ቀረጻ የሚረዱ ግብዓቶችን ያቀርባል፤
4) የኤክስፖርት የገበያ መዳረሻዎችን ከማስፋት አንጻር አለም አቀፍ ኤክስፖዎችን ባዛሮችን፣ ኤግዚቢሽኖችንና ሲምፖዚየሞችን ከሚመለከታቸው ጋር በማዘጋጀት የማስተዋወቅ ስራ ያከናውናል፤
5) ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ድጋፍ ያደርጋል።

# ክፍል ስድስ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

42.**የተከለከሉ ተግባራት፡-**

በዚህ መመሪያ እና በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ህጎች መሠረት የተቀመጡ ክልከላዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈፀም የተከለከለ ነው፡-

1) የብቃት ማረጋገጫና የጸና የንግድ ፍቃድ ሳይኖረው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን መነገድ፤
2) በአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ግብይት ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው አግባብ ያለው ሴክተር መሥሪያ ቤት ካወጣው የቴክኒክ አሠራር ውጭ አትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ማዘጋጀት፤
3) በአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ግብይት ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል ወይም የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን መሸጫነት ከተዘጋጀ ቦታ ውጪ መሸጥም ሆነ መግዛት፤
4) የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ንጽህናው በጎደለ መጋዘን ማከማቸት፣ማጓጓዝ እና ማዘጋጀት፣
5) በአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ግብይት ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው

የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን እንዲያከማች ከተፈቀደለት መጋዘን ውጭ ማከማቸት፤

6) በአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች የማጓጓዝ ሥራ ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ንጽህና በጎደለው ሁኔታ ወይም ህጋዊ ፈቃድ በሌለው ተሽከርካሪ ማጓጓዝ፤

7) በአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ግብይት ላይ የተሰማራ ወይም ከአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ግብይት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ባለው ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ያለአግባብ ጥቅም ለማግኘት ሆነ ብሎ አሳሳች ድርጊት መፈጸም፤

8) የሃገሪቱን የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ስም የሚያጎድፍ ማንኛውንም ድርጊት መፈጸም፤

9) በአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ግብይት ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው የገባውን ውል በውሉ መሰረት ያለመፈፀም፤

10) በተቆጣጣሪ ወይም ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት የሚጠየቀውን መረጃ ያለመስጠት ወይም የተጭበረበረና የተዛባ መረጃ የመስጠት፡፡

### 43. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

**አስተዳደራዊ እርምጃዎች** በተመለከተ ሚኒስቴሩ እና የግብይት ጥራት እንዲቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው አግባብ ያለው የክልል አካል ባወጣቸው ህጎች መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 44. ስለ ቅሬታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ

1) ዓላማ

የግብይት ተሳታፊዎች ቅሬታ የማስተናገጃ ሥርዓት ዓላማ፡-

ሀ) ለቅሬታዎች አፋጣኝ መፍትሄ ለመስጠት፤
ለ) ለቅሬታዎች መንስዔ ሊሆኑ የሚችሉ ስህተቶችንና ለማረም፤ እና
ሀ) ሁሉንም በእኩልነት ለማስተናገድ የሚያስችል ቀልጣፋ ፍትሐዊ የሆነ አሠራር በማስፈን የሰመረ ግብይት እንዲዳብር ማድረግ ይሆናል፡፡

2) ቅሬታ የማቅረብ መብት

ሀ) ማናቸውም የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ተዋናዮች በሚፈጽሙት የግብይት ሂደት አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት ከመሄዳቸው በፊት ቅሬታቸውን በመግባባት በውይት እንዲፈቱ ይበረታታሉ፤
ለ) ቅሬታቸውን በመግባባት በውይይት መፍታት ካልቻሉ በጋራ በመረጡት አደራዳሪ በኩል አቅርበው በድርድር ለመፍታትት ጥረት ያደርጋሉ፤
ሐ) በተራ ቁጥር ለ) መሰረት አለመግባባቶች መፈታት ካልቻሉ ጉዳዩን በመደበኛ ፍርድቤት ማቅረብ ይችላል።

- **ስለ ጥቆማ አሰጣጥ**

1) የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ምርት ግብይት ላይ ጉዳት መድረሱን ወይም ማናቸውም ሕገ ወጥ ድርጊት መፈጸሙን ያወቀ ማንኛውም ሰው በአካባቢው ለሚገኝ ግብይት ለሚያስተዳድር አካል ወይም አግባብነት ላለው የመንግሥት አካል መጠቆም አለበት፤
2) በግብይት ሂደት ህገ ወጥ ድርጊት መፈጸሙን ጠቁሞ ያስያዘ ማንኛውም ሰው ጉዳት ያደረሰው ግለሰብ ከሚቀጣው ቅጣት ገንዘብ 30 (ሰላሳ) በመቶ ማበረታቻ እንዲከፈለዉ ይደረጋል

## 45. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም መመሪያና ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፣

## 46. የመተባበር ግዴታ

1) ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ በማስፈጸም ረገድ ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፤
2) የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ስራስር ግብይት ተቆጣጣሪ ህገወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን የአትክልት፣ ስራስርና ፍራፍሬ ምርት ለመያዝ በሚያደርገው እንቅስቃሴ በየደረጃው የሚገኙ የጸጥታ እና የሚመለከታቸዉ የመስተዳድር አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

## 47. መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፫/፪ሺ፲፪ መሰረት በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በፍትህ ሚኒስቴር እና በሚኒስቴሩ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ …. ቀን 2015 ዓ.ም.**

**ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)**

**የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር**